የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY
☎ 55 35 06, 55 17 89, 12 39 00 - Fax 251-1-55 31 55 - ✉ 882
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ - Addis Ababa, Ethiopia

ቁጥር
Ref. No. መኢአ/3/355/2001
ቀን
Date 19/12/2001

# ከድጡ ወደ ማጡ . . .

## ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የተሰጠ መግለጫ

ከ18 ዓመት የሕወሐት /ኢህአዴግ/ አገዛዝ በኋላ አገሪቱ ዛሬም በዘረኝነት አዚም እየታመሰችና ወደ ጠቅላላ አለመግባባት ወደሚያሸጋግሩ አፍራሽ አዝማሚያዎች እያመራች እንደሆነ የሚያመለክቱ ሁኔታዎች በየአቅጣጫው እየታዩ ናቸው፡፡

ኢህአዴግ በጠመንጃ ኃይል ደርግን አስወግዶ ሥልጣን ሲይዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥርጣሬና ተስፋ በተቀላቀለበት መንፈስ ይመለከተው እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ የሕዝቡ ደስታ የደርግ መውደቅና የተጠበቀው የእርስ በርስ መተላለቅ ተወግዶ በተረጋጋ ሁኔታ የመንግሥት ለውጥ መደረጉ ሲሆን ከጅምሩ ጀምሮ ሕዝቡ አጥብቆ የተቃወመው የአገሪቱን የአስተዳደር መዋቅር በዘርና በቋንቋ መከፋፈሉን ነበር፡፡

በእርግጥም ድብዙ ብሔር ብሔረሰቦች እናት የሆነችው ኢትዮጵያ የውስጥ የአስተዳደር ወሰን በዘርና በቋንቋ ክንድ ከፋፍሎ ማዋቀር በየወቅቱና በየምክንያቱ የሚፈነዳ ፈንጅ እንደመቅበር የሚቆጠር መሆኑን በማስረዳት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማሕበራዊ ሕይወት ጠበብቶች ሳይቀሩ ለኢህአዴግ ምክር እንደሰጡ እናታውሳለን፡፡

የሕዝብን አስተያየትና የአዋቂዎችንም ምክር ለመቀበል ያልታደለው ኢህአዴግ ግን የብሔር ብሔረሰቦችን መብት ለማስከበር ነው በሚል ሰበብ የአገሪቱን የውስጥ አስተዳደር በዘርና በቋንቋ ወሰን ማዋቀር የሕዝቡን እድገት ያፋጥናል ብሎ እንደሚያምን ሲገልጽ ነበር፡፡ ሆኖም የኢሕአደግ አገዛዝ ከተጀመረ እነሆ ከ18 ዓመት በላይ ያለፈ ሲሆን ድህነቱም ችግሩም የእርስ በርስ ግጭቱም የበለጠ እየከፋ እንጂ የተሻለ ነገር አልታየም፡፡

በመሠረቱ ለኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መብት መከበር ሁላችንም ቅድሚያ ሰጥተን የምንታገልለት ዋና ጉዳይ ነው፡፡ የብሔረሰቦች መብት የሚከበረውም የውስጥ አስተዳደሮችን በዘርና በቋንቋ በመከፋፈል ሳይሆን ዲሞክራሲያዊና ሕዝባዊ የሕዝብ አስተዳደር በመዘርጋት መሆኑን ላለፉት 18 ዓመታት ሳናሰልስ አስረድተናል፡፡ ኢሕአዲግ ግን ከራሱ ድምፅ በቀር የሌላውን መስማት ስለማይፈልግ ዛሬም በዚህ መንገድ በመቀጠሉ ከሁሉም የከፋው አካባቢን ከዘር የማፅዳት አዝማሚያ በአሁኑ ጊዜ እየተከሰተ መሆኑ ለዚህ ትልቅ ማስረጃው ድርጊቶቹ አሁንም መቀጠላቸው ነው፡፡

ከአሥርና ከአሥራ አምስት አመት በፊት በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ በቤንች ማጂ ዞን በሺ የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች በዞኑ አስተዳደር አስተባባሪነት ከመህልና ከሰሜን ኢትዮጵያ ሕገ መንግሥቱ በሚፈቅድላቸው መሰረት የተንቀሳቀሱ ኢትዮጵያውያን በቤንች ማጂ ዞን መንደር መስርተው ለመንግሥት ግብር እየከፈሉ በእርሻ ሥራ መኖር



E-mail: lion@telecom.net.et

እንደጀመሩ ይታወቃል፡፡ ከነዚህ ሠፋሪ አርሶ አደሮች መካከል በምርጥ አምራችነት ከመንግሥት ሽልማትና ምሥጋና የተቀበሉ ይገኙበታል፡፡ ባለመታደል እነዚህ አርሶ አደሮች በአሁኑ ጊዜ ከመኖሪያ መንደራቸው በዚህ በክረምት ወራት ተፈናቀለው ከነቤተሰቦቻቸው መድረሻ አጥተው ከፊሉ በአዲስ አበባ ከተማ በየአደባባዩ ሲንገላቱ ይታያል፡፡

ለኢትዮጵያውያን መፈናቀል አዲስ ነገር ባይሆንም "የአካባቢው ተወላጅ አይደለህም!!" በመባል በዚህ በእርሻ ወቅት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ከመኖሪያ መንደራቸው ተፈናቀለው ከእነቤተሰቦቻቸው መድረሻ አጥተውመንከራተታቸው የሚጠቁመው ነገር ቢኖር በአገራችን ጤናማ ሁኔታ ያለመኖሩን ነው::

አንዱ አካባቢ ሲራቆት ወደ ሌላው አካባቢ እየሄደ ከየአካባቢው ተወላጅ ጋር ተዋህዶ መኖር በኢትዮጵያ የተጀመረው ዛሬ አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ ሕዝብ የአኗኗርና የአስፋፈር ልምድ በዘር አጥር መካከልና "መጤና ተወላጅ" በሚል የባዕድ መንፈስ መናቆር በአገራችን ያልተለመደ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአካባቢው የመንግሥት ባለስልጣኖች ጭምር ሕዝቡን "መጤ" እያሉ የማፈናቀል ተግባሩ በአካባቢው ባለሥልጣናት እንደገና ከ15 ዓመት በኋላ በአዲስ ሥልት መጀመሩ ለአገሪቱ ጤናማ ምልክት አለመሆኑ ሁሉንም ዜጋ ከልብ የሚያሳዝንና የሚያጠያይቅ ሆኗል፡፡

ከመኖሪያ መንደራቸው የተፈናቀሉት እነዚህ አርሶ አደሮች ቤንች ማጂ ዞን መኖር ከጀመሩ ጀምሮ በሰላማዊ ኗሪነት በእርሻ የሚተዳደሩ ሲሆኑ በራስ አገዝ ፕሮግራም መኖር መጀመራቸው በኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት እና በአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣኖችም የተደገፈ ነበር፡፡ ለመጥቀስ ከተፈለገም የኢትዮጵያ ሕገመንግሥት አንቀጽ 32 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፈለገው አካባቢ ተዘዋውሮ የመኖርና የመስራት ነፃነትና መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡

ይህም በመሆኑ አርሶ አደሮቹ አካባቢውን አልምተው ኑሮአቸውን አሸንፈው ትርፍ አምራች በሆኑበት ባለፉት ዓመታት ውስጥ ከአካባቢው የመንግስት ተቋም ድጋፍ ይሰጣቸው እንደነበር እና የራሳቸውን ደህንነት የሚጠብቁበት መሳሪያ እየገዙ በግል እንዲታጠቁ ከመንግሥት ተፈቀደላቸው እንደነበርም ይገልጻሉ፡፡ ድጋፍ ማጣት የጀመሩትና በአካባቢው ባለሥልጣኖች በየምክንያቱ መታሰርና መጎሳቀል የጀመሩት ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በኋላ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ስለዚህም የ2002 ምርጫ ሲቃረብ "መጤዎች መሬትህን ሊያስለቅቁህ ነው?" የሚል ቅስቀሳ ተጀመረ፡፡

በመጀመሪያ በሕዳር ወር 2001 ዓ.ም በቤንች ማጂ ዞን 8 ወረዳዎች ውስጥ በእርሻ ሥራ ላይ የተሰማሩትንና ባለፉት አስርና 15 ዓመታት ከአካባቢው ተወላጆች ጋር ተሰባጥረው በልደትና በጋብቻ ተዋህደው የሚኖሩትን በነሱ አጠራር "መጤ" የሚሏቸውን ኢትዮጵያውን በትዕዛዝ አሰባስበው አካባቢውን በ8 ቀን ውስጥ ለቀው እንዲሄዱ ትዕዛዝ ሰጧቸው፡፡ ይህን ትዕዛዝ ያልፈፀመ አርሶ አደር እርምጃ እንደሚወሰድበትም ከበላይ የመንግሥት አካል ትዕዛዝ የመጣ መሆኑን ለአርሶ አደሮቹ ተገለፀላቸው::

ለአርሶ አደሮቹ ይህ ትዕዛዝ በተነገረ ጊዜ ምን አደረግን? የትስ እንወድቃለን? የዘራነውንስ እህል ምን እናደርግዋለን? በአልጋ ላይ የሚገኙ በሽተኞችና አራሶችንስ የት እንጥላቸዋለን? የሚል ጥያቄ ቢያቀርቡም፡፡ ለዚህ ጥያቄ አንድ የአካባቢው ተወላጅ የሆነ



የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ" ALL ETHIOPIAN UNITY PARTY (AEUP)

ባለስልጣን የሰጠው መልስ "የእናንተ አያቶች የእኛን አያቶች በባርነት ገዝተዋል እናንተ ዛሬ በሐብት እየተደራጃችሁ ስለሆነ እንደገና ነገ የእኛን ልጆች ልትገዙ እየተዘጋጃችሁ ስለሆነ ከዚህ አካባቢ መባረር አለባችሁ..." የሚል ቃል እንደነበር አርሶ አደሮቹ ይገልፃሉ። በዚሁ ጊዜ ሌሎችም ምክንያቶች ከባለስልጣኖቹ ተደርድረዋል። ከነዚህም ጥቂቶቹ "በደቡብ ክልል የአማራ ዞን ለመመስረት ከብአዴን ጋር ተነጋግራችኋል፣ የአማራ ክልል ሕዝብ ቁጥር የቀነሰው የእናንተ ወደ ደቡብ በመምጣቱ ነው። ደን ትጨፈጭፋላችሁ ተብሎ እንደተነገራቸው ታወቋል።

እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ከተጨባጩ እውነታ ጋር አብረው የማይሄዱ ናቸው። አርሶ አደሮቹንም ለማፈናቀል በቂ ሕጋዊ ምክንያት አይደሉም ከእውነታውም ጋር አይጣጣምም ለምሳሌ ከተፈናቃዮቹ መካከል አብዛኛዎቹ እዚያው የተወለዱና እዚያው አድገው ተድረው ኑሮአቸውን የጀመሩ ይገኙበታል። ከዚያ አካባቢ ውጭ ሌላ የትውልድ ቦታ አያውቁም ወዴት ሊሄዱ ይችላሉ? ከዚህ በቀር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢ በሰላማዊ መንገድ ሰርቶ መኖር እንደሚችል በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት የተከበረ መብት ስላለው ይህን መብቱን የሚገፈው ማነው? ይህ ሕገ-መንግሥታዊ መብቱ እንዳይጣስ የሚከላከልለትስ ማነው? የሚሉ ጥያቄዎች በማንኛውም ሰው አእምሮ ሊነሱ ይችላሉ።

በዚህም ጊዜ ትልቁ ችግር አፈናቃዮቹ የመንግሥት አካል መሆናቸውና መንግሥትም አቤቱታውን ሰምቶ አፋጣኝ እርምጃ አለመውሰዱ ነው። ዋናው ጥያቄም በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 32 ላይ የተገለፀው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም ስፍራ ተዘዋውሮ የመኖርና የመስራት መብቱ ሲደፈር ገገርው ፓርቲና መንግስት ዝም ብለው መመልከታቸውና የእርምት እርምጃ ያለመውሰዳቸው ሚስጢር ምን እንደሆነ ግልፅ ያለመሆኑ ነው።

ኢትዮጵያውያን እንደ ባእድ አገር ተወላጆች ንብረታቸውን የትም በትነው የተከፈተ ቤታቸውን ሳይዘጉ ለዓመታት ከኖሩበት አካባቢ በመጤነት ስም መባረራቸውና ይህም ድርጊት በመንግሥት አካላት መፈፀሙ የበለጠ አሳዛኝና አጠያያቂ ነው። ታሪክም ይቅር የማይለው ወንጀል ነው። ያም ሆነ ይህ ድርጊቱም አንድ ጊዜ ተፈፅሞ የቆመ ሳይሆን አሁንም እየቀጠለ መሄዱ የበለጠ አሳዛኝ ነው።

በዚህ ሁኔታ ከሐምሌ 8 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ በሺህ የሚቆጠሩ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸው መኖሪያቸውንና ንብረታቸውን ሳያሰባስቡ የተከፈተውን መኖሪያ ቤታቸውን ሳይዘጉ ከቤንች ማጂ ዞን እንዲባረሩ ተደርጓል። አሁንም እየቀጠለ ነው ከተፈናቀሉት ከእነዚህ አርሶ አደሮች ከፊሉ አዲስ አበባ ከደረሱ በኋላ በመጀመሪያው ቀን በየአደባባዮ ሰፍረው ለፀሐይና ለዝናብ ተዳርገው አይተናል። ከተወሰነ ጊዜ በኋላም አዲስ ከተማ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ እንዲገቡ ተደርጎ ነበር ተዘግቶባቸው የዕለት ምግብ ዕርዳታ ከሚሰጡ ሰዎች ጋር እንኳን እንዳይገናኙ ተደርጓል። አዲስ አበባ ያልደረሱት ሌሎቹ ተፈናቀዮች ዳግም እግራቸው እንደመራቸው በየአቅጣጫው ስለተበተኑ በአሁኑ ጊዜ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ማወቅ አልተቻለም።

በዚህ ድርጊት አርሶ አደሮቹ ከነቤተሰባቸው ያለ መጠለያ በፀሐይና በዝናብ ሲሰቃዩ፣ ነፍስ ጡሮች በየመንገዱና በየአደባባዩ እየወለዱ ለዚች አለም አዲስ የሆኑት አራስ ሕጻናት ሳይቀሩ የግፉ ተቋዳሽ ሆነው ለሚመለከት ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ ከዚህ የበለጠ

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ"
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)

የሚያሳዝነው ነገር እንደሌለ ግልጽ ነው። ኢትዮጵያዊያን በሀገራቸው ስደተኛ ተብለው እንደገና ሲሰደዱ ማየትም የሚያሳዝን ነው።

ሀገራችን በምግብ ምርት እጥረት ችግር ተወጥራ ሕዝቡ በረሃብ እየተሰቃየ በሚገኙበት በአሁኑ ጊዜ አርሶ አደሩ ምርታማ እንደሆን ድጋፍ ከመስጠት ይልቅ መጪውንም ዓመት የበለጠ የረሀብ ዘመን ለማድረግ ይህ አፍራሽ ሥራ በመንግሥት አካላት መፈፀሙና በየማሳው ላይ የሚገኘው የተፈናቃይ አርሶ አደሮች የተለያዩ አዝእርቶችና እንስሶች የአውሬ መፈንጫ መሆናቸው የበለጠ የሚያሳዝን ነው።

ከዚህም በቀር ከመኖሪያቸው እንዲፈናቀሉ የተደረጉት አርሶ አደሮች ብዙ ግፍ እንደተፈፀመባቸው ይገልፃሉ። ቤታችንን ለቀን አንሄድም ያሉ አርሶአደሮች ተደብድበዋል፣ በአፍንጫቸው እስኪ.ረብቶ እየተሻጠ እንዲሰቃዩ ተደርጓል፣ አንዳንዶቹም በጆንያ ውስጥ እንደቃ እንዲታሰሩ እየተደረገ በሜዳ ላይ እንዲንከባለሉ መደረጉን ይገልጻሉ። ጉንጫቸው በሳንጃ እየተተለተለ ጥርሳቸው እንዲወልቅ የተደረጉ እንዳሉም ይናገራሉ። ይህ ከተፈፀመባቸው በኃላ እንዲታሠሩ የተደረጉትት በርካታ አርሶ አደሮች ምግብ እና መፀዳጃ ተከልክለው እንዲሰቃዩ ተደርጓል። በአጠቃላይ ድርጊቱ ከሞራልም ከሕግም ከሰብአዊነትም አንጻር ሲታይ አሰቃቂ፣ አስደንጋጭና የሰው አእምሮ ሊሸከመው የማይችል በፍፁም ሕገ ወጥ የሆነ ሥራ ነው።

አርሶ አደሮቹ ድርጊቱን በመዘርዘር ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ፣ ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት፣ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ለፌደራል ፖሊስ፣ ለባአዴን ጽ/ቤት፣ ለአማራ ክልላዊ መንግሥት /በስልክ/፣ለደቡብ ክልል መንግሥት /በስልክ/ አመልክተዋል። ሆኖም ችግሩን ለማስወገድ ምንም ዓይነት እርምጃ አልተወሰደም።

የድርጊቱ አስፈጻሚ መመሪያ ሰጪና የአፈፃፀሙ ስልት አቀናባሪ በመሆንም ጭምር በሕግ የሚጠየቁ የመንግሥት ባለሥልጣናት እንደሚኖሩ እናምናለን ድርጊቱ ከዘር ማፅዳት ጋር የተያየዘና ዓለማውም የዚህ መንፈስ ግብ እንዳለው የሚያሳዩ ምልክቶችም ስላሉ በእንጭጩ መፍትሔ እንዲያገኝ ማድረግ የማዕከላዊ መንግሥት ኃላፊነት እንደሆነ ግልፅ ነው። ድርጊቱ በወቅቱ ካልታረመና በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ ካልተወሰደ ሀገሪቱን ወዳልተጠበቀ አደጋ ሊመራት የሚችል የመጨረሻው መጀመሪያ የሆነ የአጥፊነት ሥራ መሆኑ ጎልቶ ይታያል።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የአገሪቱ ችግሮች እስከዚህ ደረጃ ሲደርሱና ዋናው የጥፋት መንገድ በግልጽ ሲጀመር በዝምታ የሚመለከትና ከጥፋት በኂላ በተጠያቂዎች ላይ ማስረጃ የመደርደር ፍላጐትና ዓላማ የለውም። ዓላማው ለወገንና ለሀገር በሚጠቅም ሥራ ላይ መተባበር ሀገርንና ወገንን የሚጐዳ ድርጊት ሲፈፀም በአፋጣኝ እንዲታረም ለሚመለከተው ሁሉ ማሳወቅ ግዴታው ነው። “የአካባቢው ተወላጅ አይደለህም” በሚል ምክንያት የተጀመረው ሕዝብን የማፈናቀል ሕገ-ወጥ ሥራ በተለይ በአካባቢ የመንግሥት ባለሥልጣናት መፈፀም መጀመሩ ለአገራችን የአደጋ ምልክት ነው። ስለሆኘም ይህች ያልታደለች አገራችን “ከድጡ ወደ ማጡ” እያመራች መሆኑን ለአገር ወዳድና ለሠላም አፍቃሪው የዓለም ሕዝብ ማሳወቅ ግዴታችን ይሆናል።

በአጠቃላይ ማንኛውም የአገራችን ጉዳይ ከሕጋዊ ማዕቀፍ ሳይወጣ ሰላማዊ ትግሉ እንዲቀጥልና ለአገር የሚበጁ ተግባራት እንዲሰፍን በማድረግ ረገድ መኢአድ የበኩሉን

አስተዋጽኦ ከማድረግ ወደ ኋላ አይልም። እንዲህ ያሉት የዕብደት መሰል ሥራዎች ሲፈፀሙም ለመንግሥትና ለሕብረተሰቡ በመግልፅ በአገሪቱ ውስጥ ሕግና ሥርዓት የማስከበር ኀላፊነት ያለበት የመንግሥት አካል ኃላፊነቱን እንዲወጣ ከማሳሰብ አይቆጠብም።

ስለሆነም ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት በስልክ ጉዳዩን ለማስረዳት ብንሞክር "ከእናንተ ጋር እንነጋገርም" የሚል መልስ መሰጠቱ የበለጠ አሳዝኖናል። ከዚህም በቀር ለማዕከላዊ መንግስት የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትርም ለማስረዳት ቀጠሮ ጠይቀን ተቀባይነት አላገኘንም። ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ በቤንች ማጂ ዞንና በአካባቢው ባለስልጣኖች የተፈፀመውንና በሁሉም ደረጃ በሚገኙ የኢህአዴግ መንግሥት ባለስልጣኖች ዝምታ ተደግፎ ከዘር ማጽዳት ጋር በተያየዘ መንፈስ አርሶ አደሩ ከኖረበት እንዲፈናቀል በማድረግ የሚፈፀመው በደል በአስቸኳይ እንዲቆም እንጠይቃለን።

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ተዘዋውሮ የመስራትና የመኖር መብት እንዲከበር የማድረግ ኃላፊነቱን የኢሕአዴግ መንግሥት እንዲወጣ አጥብቀን እያሳሰብን የሚከተሉት እርምጃዎች በማዕከላዊ መንግሥት እንዲወስድባቸው እንጠይቃለን፤

1. በአካባቢው የመንግሥት ታጣቂዎች ከቤት ንብረታቸው እንዲፈናቀሉ የተደረጉትንና በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባና በሌሎችም አካባቢዎች በተፈናቃይነት ሲንገላቱ የሚታዩትን በአስቸኳይ ወደ መኖሪያ መንደራቸው እንዲመለሱና ተግባራቸውን በተረጋጋ መንፈስ እንዲቀጥሉ የሚያደርግ እርምጃና ጥበቃ እንዲደረግላቸው።
2. የመኖሪያ ቤታችንን አንለቅም በማለታቸው በአካባቢው የመንግሥት ባለስልጣኖችና ታጣቂዎች ተይዘውና ታስረው የሚንገላቱት አርሶ አደሮች በነጻ ተለቀው ወደ ቀድሞ መኖሪያ ቤታቸው እንዲመለሱ እንዲደረግ እና ጥብቃም እንዲደረግላቸው፡-
3. በታጣቂዎች ተገደው ቤት ንብረታቸውን ትተው በሄዱበት ወቅት የተዘረፈውንና የጠፋውን የአርሶ አደሮቹ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት እንዲመለስ ወይም እንዲተካላቸው ለደረሰባቸውም እንግልት ካሳ እንዲሆን የመልሶ ማቋቋም ሥራ እንዲካሄድላቸውና ይህንንም የሚያስፈጽም የመልሶ ማቋቋም ኮሚቴ አንዲቋቋምና ስራውን በአስቸኳይ እንዲጀምር እንዲደረግ፡-
4. ይህን ሕገ ወጥ ተግባር ከማቀድ ጀምሮ ድርጊቱን በመፈፀምና በማስፈፀም የተካፈሉና አቤቱታም ሲቀርብላቸው የበኩላቸውን ኃላፊነት ያልተወጡ የመንግሥትና የገዢው የፓርቲ ባለስልጣኖች በሕግ ፊት ቀርበው ተገቢውን የማረሚያ ውሳኔ እንዲሰጣቸውና ይህም ለመፈፀሙ ለሕብረተሰቡ በይፋ እንዲገለፅ እንጠይቃለን።

- የሕዝቦች ሰብአዊ መብት በትግላችን ይከበራል፣
- የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ የመኖር መብቱ ይከበራል።

**የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)**
**መአከላዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ**
**ነሐሴ 2001 ዓ.ም**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)